
ነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን
Petroleum & Energy Authority

የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን

- ማደያ በሌለባቸው ከተሞች እና አከባቢዎች የነዳጅ የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ አሰጣጥና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር...../2014 ዓ/ም

2014 ዓ/ም

1.አውጪው ባለሥልጣን

- የፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት ለንግድና ቀጣናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር አንቀጽ 5(1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

2.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “ማደያ በሌለባቸው ከተሞች እና አከባቢዎች የነዳጅ የችርቻሮ ፈቃድ አሰጣጥና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር...../2014 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

- የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣንን ሥልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው ደንብ ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1/ “መመሪያ” ማለት ማደያ በሌለባቸው ከተሞች እና አከባቢዎች የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ፈቃድ አሰጣጥ እና የቁጥጥር መመሪያ ነው፣

2/ “የብቃት ማረጋገጫ” ማለት የነዳጅ ውጤቶች መያዣ፣ ማከማቻ፣ ማጓጓዣ እና የችርቻሮ መሸጫ መስፈሪያና የደህንነት መጠበቂያ ብቃትን በማረጋገጥ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው።

3/ “ባለድርሻ አካላት” ማለት የክልል እና የከተማ አስተዳደር በተዋረድ ያሉ ንግድን የሚመሩ አካላትና ማደያዎች ናቸው።

4/ “የነዳጅ ችርቻሪ ነጋዴ” ማለት መደበኛ የነዳጅ ማደያ መሠረተ ልማት በሌለባቸው ከተሞችና አከባቢዎች የነዳጅ ውጤቶችን እያቀረበ በችርቻሮ እንዲሸጥ የተፈቀደለት ድርጅት ወይም ሰው ነው፤

4 የመመሪያው አስፈላጊነት

- የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተሞች የሚደረገው የነዳጅ ችርቻሮ ንግድ የሚመራበት፣ የነዳጅ ዋጋ የሚወሰንበት፣ ቁጥጥር የሚደረግበትና የአከባቢ ደህንነት የሚጠበቅበት የአሠራር ሥርዓት ባለመኖሩ ለተጠቃሚው የሚቀርበው ነዳጅ ተገቢ ባልሆነ ዋጋ እና በህገወጥ ንግድ መልክ የሚሰራ በመሆኑ ይህንኑ የአሠራር ክፍተት ለመሙላት ታስቦ የተዘጋጀ መመሪያ ነው።

5.የተፈጻሚነት ወሰን

- ይህ መመሪያ በነዳጅ ማደያ እና ከማደያ በታች በነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ ላይ በሚሳተፉና ይህንን ተግባር በሚያስፈጽሙ ተቆጣጣሪ አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

6. አግባብነት ያላቸው ተቆጣጣሪ አካላት ተግባር

6.1 ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የሚከተሉትን ግባራት ያከናውናል፡-

1. የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ንግድ ሕጋዊ ሥርዓቱን ተከትሎ መከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
2. የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድን የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት አንዲከታተሉት ያስተባብራል፣በሥራ ሂደት ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፣

የቀጠለ

3. ማደያ በሌለባቸው ከተሞች እና አካባቢዎች የሚደረገውን የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ቀመር አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል ሲወሰን ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤
4. ማደያ በሌለባቸው የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ሲተመን መሠረት የሚደረገው የማደያ መሸጫ ዋጋ፣ የትራንስፖርት (አስፖልት /ጠጠር)፣ የመጫኛና የማራገፊያ ወጪ፣ ብክነትና ትነት፣ የችርቻሪው የትርፍ ህዳግን ያካትታል፣
5. ማደያ በሌለባቸው ከተሞች የነዳጅ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በሚከተለው ቀመር ይሰላል፣

የቀጠለ

ሀ. ከማደያ መግዣ ዋጋ (1)

ለ. የትራንስፖርት ወጪ (2)

. በአስፋልት መንገድ ---------- ብር 0.008/ኪ/ሜ/ሊትር

. በጠጠር መንገድ ---------- ብር 0.01/ኪ/ሜ/ሊትር

ሐ. የማስጫኛና ማውረጃ ወጪ (3) --------- ብር 0.10/ሊትር

መ. የብክነትና ትነት ወጪ (4) ---------- ብር 0.02/ሊትር

ሠ. የቸርቻሪ የትርፍ ህዳግ ---------- [(ሀ)+(ለ)+(ሐ)+(መ)]*5 በመቶ

6. የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ ላይ የሚሳተፉ ተቋማትን የትርፍ ሕዳግ ቀመር ማሻሻል ሲያስፈልግ አዘጋጅቶ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲወሰን ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣
7. መመሪያውን ያላከበሩ ወይም የጣሱ የነዳጅ ውጤቶች ቸርቻሪዎች ላይ አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣
8. በህገ ወጥ መንገድ ሲጓጓዝ ወይም ተከማችቶ የተገኘ የነዳጅ ውጤቶች በመንግሥት እንዲወረስ ያደርጋል፣

1. ማደያ በሌለባቸው ከተሞች እና አካባቢዎች የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ የተፈቀደላቸው ድርጅቶች እና ግለሰቦች በአካባቢው ለሚገኙ ህብረተሰብ በትክክል ስለመሸጣቸው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ ያደርጋሉ፣
2. የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ተመን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚወሰነው ቀመር መሠረት በትክክል መሠራቱን የክትትልና የቁጥጥር ተግባራትን ያከናውናሉ፣
3. የነዳጅ ችርቻሪ ነጋዴው ለተጠቃሚዎች የሚያቀርበውን የነዳጅ ውጤቶች ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር ቀላቅሎ እንዳይሸጥ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ ያደርጋሉ፣
4. የነዳጅ ውጤቶችን የችርቻሮ ንግድ አፈጻጸም መረጃዎችን በማደራጀት በየወሩ ለባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ሪፖርት ያደርጋሉ፣
5. የነዳጅ ማደያ መሠረተ ልማት እንዲስፋፋ ተግቢውን ድጋፍ ያደርጋሉ።

6.3 በዞን ንግድ መምሪያዎች በነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ ቁጥጥር ላይ የሚከናወኑ ተግባራት፣

1. የነዳጅ ቸርቻሪ ነጋዴ የገዛውን የነዳጅ ውጤቶች ጥራቱና ደህንነቱ ጠብቆ በተተመነው ዋጋ ለአከባቢው ህብረተሰብ መሸጡን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣
2. የነዳጅ ማደያ የሌለባቸውን ከተሞችና አካባቢዎችን በመለየት ለክልልና ለባሥልጣን መ/ቤቱ ያሳውቃል፤
3. የነዳጅ ችርቻሮ ፈቃድ ለማግኘት ማደያ ካለበት ቢያንስ 20 ኪሎ ሜትር መራቅ አለበት፤
4. ማደያ የሌለባቸው ከተሞችንና አከባቢዎች ቅርብ ከሆኑ ማደያዎች ጋር ያስተሳስራል፣

የጠለቀ

5. ከየወረደው የሚቀርብለትን የነዳጅ ፍላጎት መሠረት በማድረግ ማደያ በሌለባቸው ከተማና አከባቢ ነዳጅ በችርቻሮ እንዲቀርብ የአቅርቦት መጠንን መሠረት ያደረገ የነዳጅ ቸርቻሪ ብዛት ይወስናል፣

6. ነዳጅ ቸርቻሪው ለተፈቀደለት ከተማና አከባቢ ፍጆታ ብቻ የሚውል ነዳጅ ከማደያው እንዲሸጥለት ትሥሥር ይፈጥራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

7. ማደያ በሌለባቸው ቦታዎች ማደያ መገንባት ለሚፈልጉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የግንባታ ቦታ እና ኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፣

8. የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ግብይት አፈጻጸም ሪፖርት ከማደያ፣ ከቸርቻሪውና ከወረዳው መረጃ በመሰበሰብና በማደራጀት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ቅጽ 2 መሠረት በየወሩ ለክልል ሪፖርት ያቀርባል፣

የጠለቀ

9. የነዳጅ ውጤቶችን በችርቻሮ እንዲያቀርቡ ለተፈቀደላቸው ቸርቻሪዎች ወርሀዊ የነዳጅ ፍላጎት ዓይነትና መጠን በመጥቀስ እንዲሸጥላቸው ትሥሥር ለተደረገላቸው ማደያዎች ያሳውቃሉ።

10 .ለነዳጅ ውጤቶች ቸርቻሪ ነጋዴ ስለነዳጅ አያያዝና ደህንነት በተመለከተ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት አለበት።

6.4 በወረዳ ንግድ ጽ/ቤቶች የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድን ለመቆጣጠር የሚከናወኑ ተግባራት፣

1. በወረዳው የሚገኙትን የነዳጅ ውጤቶች የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች፣ ኢንዱስትሪዎች (ወፍጮ) ጄኔሬተሮችና ሌሎች የነዳጅ ውጤቶችን ፍላጎት ዓይነትና መጠን አጥንቶ ለዞኑ ያቀርባሉ፣

የጠለቀ

2. የነዳጅ ችርቻሮ ፈቃድ ለሚጠይቁ ቸርቻሪ ነጋዴዎች ለወረዳው ከሚያስፈልገው የነዳጅ መጠን ውስጥ ለአከባቢው መቅረብ የሚገባውን የነዳጅ መጠን በመወሰን የድጋፍ ደብዳቤ ለዞኑ ይጽፋሉ፣
3. የነዳጅ ቸርቻሪው ነጋዴ ከተፈቀደለት ማደያ የገዛውን የነዳጅ ውጤቶች ለተፈቀደለት ከተማ እና አከባቢ ብቻ ማቅረቡንና ለተጠቀሚው ህብረተሰብ መሸጡን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
4. ከማደያ እና ከነዳጅ ቸርቻሪው ነጋዴ በወር ውስጥ የተገዛውንና የተሸጠውን ነዳጅ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ቅጽ 2 መሠረት መረጃ በመሰብሰብ ያደራጃል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በየወሩ ለዞን ሪፖርት ያቀርባል፣

የጠለቀ

5. ማደያ በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች ማደያ መገንባት ለሚፈልጉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የግንባታ ቦታ እና ኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፣
6. ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት መሰረት መሟላቱን በማረጋገጥ የብቃት መረጋገጫ ይሰጣል፣
7. ተቆጣጣሪው የሚሰማራበት የቁጥጥር ዕቅድና መረሐግብር ያለው ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በድንገት ሊከናወን ይችላል።

7. ማደያ በሌለባቸው ከተማዎችና አካባቢዎች ለነዳጅ ችርቻሮ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፣

1. ፈቃድ ጠያቂው እንዲፈቀድለት የሚፈልገውን የነዳጅ ዓይነትና መጠን የሚገልጽ ከወረዳና ከከተማ መስተዳድር ንግድ ጽ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ለዞን ማቅረብ አለበት፣
2. የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ የሚካሄድበት ቦታ ከመኖሪያ ቤትና ከሌሎች ሱቆች የተለየ የአከባቢን ደህንነት ተጠብቆ የሚሠራበት ቦታ ስለ መሆኑ እና የመያዣ፣ የማከማቻ፣ እና የመሥፈሪያ ዕቃዎች የብቃት መረጋገጫ ሰነድ ከወረዳ ወይም ከከተማ መስተዳድር ንግድ ጽ/ቤት መቅረብ አለበት፣
3. የነዳጅ ማከማቻው የመያዝ አቅም የሚያረጋግጥ ሰነድ ከንግድ ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፤
4. አዲስ ወይም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ አለበት።

8. ማደያ በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች የነዳጅ ችርቻሪ ግዴታ

1. ከማደያ የገዛውን የነደጅ ውጤቶች በዚህ መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችና ክልከላዎችን አክብሮ መሥራት አለበት፤
2. የተፈቀደለትን የነዳጅ ውጤቶች ለተፈቀደለት ከተማ/አከባቢ ብቻ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ በትክክለኛ መስፈሪያ እና በተተመነው ዋጋ መሸጥ አለበት፤
3. የገዛውንና የሸጠውን የነዳጅ መጠን እና ዓይነት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ቅጽ 3 መሠረት መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣ በየቀኑ ለወረዳው ንግድ ጽ/ቤት ሪፖርት ማቅረብ አለበት።
4. ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ለተፈቀደላቸው አካላት መተባበር አለበት፤
5. የነዳጅ ውጤቶች እንዲያቀርብለት ከተዋዋለው ማደያ ውጭ ከሌላ ማደያ መግዛትና ከተፈቀደለት የመሸጫ ቦታ ውጭ መሸጥ የተከለከለ ነው፤
6. የነዳጅ ችርቻሮ መሸጫ ቦታ ላይ በግልፅ የሚታይ የመሸጫ ዋጋና ታፔላ መለጠፍ አለበት።

9. የነዳጅ አዳይ ግዴታ

1. ፈቃድ ለተሰጠውና ትሥሥር ለተፈጠረለት ቸርቻሪ በገባው ውል መሠረት የነዳጅ ውጤቶችን ማቅረብ አለበት፤
2. ነዳጅ አዳዩ ለነዳጅ ቸርቻሪው ነጋዴ የሸጠውን የነዳጅ መጠን እና ዓይነት መረጃ በመያዝ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘ አባሪ ቅጽ 1 መሠረት በየወሩ ለወረዳና ለዞን ንግድ ቢሮዎች ሪፖርት ማቅረብ አለበት፤
3. ከተፈቀደለት እና ውል ከፈፀመው የነዳጅ ውጤቶች ቸርቻሪ ነጋዴ ውጭ ላልተፈቀደለት ለሌላ ቸርቻሪ መሸጥ በጥብቅ የተከለከለ ነው፤

1. የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ግብይትን በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰነዶቹን ፎቶ ኮፒ በማድረግ፣ ፎቶ ግራፍ በማንሳት መረጃዎችን በማሰባሰብ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት፤
2. ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሚመለከተው የአከባቢው ፖሊስ እና የፍትህ አካላት ድጋፍ መጠየቅ ይችላል፣
3. ተቆጣጠሪ ባለሙያዎች ተቆጣጣሪ ስለ መሆናቸው የሚገልፅ የመስሪያ ቤት መታወቂያ ወረቀት እና የሥራ ትእዛዝ ደብዳቤ መያዝና ቁጥጥር ለሚደረግበት ድርጅት ማሳየት አለባቸው፤
4. በቁጥጥር ሥራ ወቅት የታየውን ጉድለት ለድርጅቱ ባለቤት ወይም ህጋዊ ተወካይ የማሳወቅ እና በቁጥጥር ወቅት በታዩ ግኝቶች ላይ በቼክ ሊስቱ መሠረት መፈራረም አለባቸው፤

የቀጠለ

5. ተቆጣጣሪው አካል ለቁጥጥር ሲወጣ የቁጥጥር ተግባራትን ለማስተባበር የተመደበው አግባብ ያለው ኃላፊ ጋር ስለሚቆጣጠረው ቸርቻሪ እና ስለሚደረገው ቁጥጥር ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ቅጽ 3 መሠረት ስምምነት ያደርጋሉ፤

6. ተቆጣጣሪው አካል ባደረገው ቁጥጥር ያገኘውን ውጤት በዚህ መመሪያ አባሪ ቅጽ 3 በመሙላት ቁጥጥር ከተደረገበት ቸርቻሪ ጋር በመፈራረም ለቁጥጥር አስተባባሪው ያቀርባል፤

6. ተቆጣጣሪው አካል የቁጥጥር ተግባሩ አስገዳጅ በሆነ ምክንያት ከመንግሥት የሥራ ሰዓት ውጪ የሚያከናውን ከሆነ አግባብ ካለው ባለሥልጣን የትእዛዝ ደብዳቤ በመያዝና ቁጥጥር ለሚደረግበት ድርጅት ማሳየት አለበት።

11.አስተዳደራዊ ቅጣት

1/ የነዳጅ ችርቻሪ

ሀ) ማንኛውም ማደያ በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሪ በየቀኑ የገዛውንና የሸጠውን ነዳጅ መረጃ በማደራጀት ለወረዳ ንግድ ጽ/ቤት ሪፖርት የማያደርግ ከሆነ ወይም ለሚላኩ ተቆጣጣሪዎች የሚጠይቁትን መረጃ ለመስጠት የማይተባበር ከሆነ የፅሁፍ ማስጠንቀቅያ ይሰጠዋል፤

ለ) ማንኛውም ማደያ በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሪ የፅሁፍ ማስጠንቀቅያ ተሰጥቶት ድጋሜ ተመሳሳይ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ፣ መያዝ ያለበትን ሰነዶች ያልያዘ እንደሆነ፣ የሚሠራበት ቦታ ላይ የነዳጅ መሸጫ ዋጋ እና ታፔላ ያልለጠፈ ከሆነ፣ ከተፈቀደለት የመሸጫ ዋጋ በላይ የሸጠ እንደሆነ፣ ከተፈቀደለት የመሸጫ ቦታ ውጪ የሸጠ እንደሆነ፣ ጥራት የሌለው የነዳጅ ውጤቶች ሲሸጥ የተገኘ እንደሆነ እና ትክክለኛ ባልሆነ መሥፈሪያ ተጠቅሞ ሲሸጥ የተገኘ እንደሆነ የጥፋቱ ክብደትና ያደረሰውን ጉዳት በማየት የተሰጠው ፈቃድ ይታገዳል፣ ይሠረዛል።

ሐ) በየእርከኑ የቁጥጥር ሥራ እንዲሠራ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም አካል በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣንና በዚህ መመሪያ ላይ ከተዘረዘረው አሠራር ውጭ የቁጥጥር ሥራ ሲያከናውን የተገኘ አካል እንደየጥፋቱ ክብደት በዲሲፒሊን ሥርዓት ከመጠየቅ እስከ ከሥራ መባረር የሚያደርስ እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል።

መ) በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠ አስተዳደራዊ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀልና በፍትሐ-ብሔር ውይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል።

2/ የነዳጅ አዳይ

ሀ) ማንኛውም የነዳጅ አዳይ የሥራ አፈፃፀሙን በተመለከተ በየወሩ ለወረዳና ለዞን ሪፖርት የማያደርግ ከሆነ ወይም ለቁጥጥር የሚላኩ ተቆጣጣሪዎች የሚጠይቁትን መረጃ ለመስጠት የማይተባበር ከሆነ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

ለ) ማንኛውም የነዳጅ ውጤቶች አዳይ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ድጋሜ ተመሳሳይ ድርጊት ሲፈፅም የተገኘ እንደሆነ፣ የነዳጅ ውጤቶች እያለው የለም በማለት ቸርቻሪ ነጋዴዎችን ያስተጓጎለ እንደሆነ፣ ጥራት የሌለው የነዳጅ ውጤቶች ሲሸጥ የተገኘ እንደሆነ፣ በመንግሥት ከተተመነው የመሸጫ ዋጋ በላይ ሲሸጥ የተገኘ እንደሆነ እንደጥፋቱ ክብደትና ያደረሰው ጉዳት የተሰጠው ፈቃድ ይታገዳል /ይሠረዛል።

ሐ) በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠ አስተዳደራዊ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀልና በፍትሐ-ብሔር ውይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል።

የመተባበር ግዴታ

ተቆጣጣሪው አካል ይህን መመሪያ በማስፈፀም ሂደት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአከባቢው ፖሊስ እና የፍትህ አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

12.ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ህጎች

በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተቀመጡ ሆኖ የነዳጅና ኢነርጂ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር.....፤የወንጀል፤የፍትሐብሔር ህጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

13.መመሪያውን ስለ ማሻሻል

ነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን መመሪያው መሻሻል ይገባዋል ብሎ በሚያምንበት ጊዜ የማሻሻያ ሃሳብ አዘጋቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

14.አስፈፃሚ አካላት

ይህ መመሪያ በባለሥልጣን መ/ቤቱ /በክልል እና በከተማ አስተዳደር፤በዞን፤በወረዳ ንግድን የሚመሩ አካላት አማካይነት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

15.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት----------ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አቶ ገብረ መስቀል ጫላ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር

አዲስ አበባ

የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን

Petroleum and Energy Authority

ከማደያ ወደ ማደያ የሌለባቸው ቦታ የተላከ ነዳጅ መመዝገቢያ ቅፅ

ቅፅ 1 በማደያ የሚሞላ

የማደያው ስም..... የማደያው ባለቤት ስም..... ስልክ ቁጥር.....

ተ.ቁ	የነዳጅ ቸርቻሪው ነጋዴ ስም	የተጫነው የነዳጅ መጠን			የተጫነበት ቀን	የተጫነለት ቦታ/ቀበሌ	የነዳጅ አስረካቡው		የነዳጅ ቸርቻሪው ፊርማ	ምርመራ
		ናፍጣ	ቤንዝን	ኬሮሲን			ስም	ፊርማ		

ፎርሙን የሞላው

ያረጋገጠው ኃላፊ

ስም ፡- _____ ስም ፡-

_____

ፊርማ ፡- _____ ፊርማ ፡-

_____

ስልክ ፡- _____ ስልክ ፡-

_____

ቀን ፡- _____ ቀን ፡-

_____

የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን

Petroleum and Energy Authority

የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ግብይት አፈፃፀም ሪፖርት

ቅፅ 2በዞን የሚሞላ

ተ.ቁ	የማደያው ስም	የቸርቻሪው ነጋዴ አድራሻ				የተጫነው የነዳጅ መጠን			የተሸጠው የነዳጅ መጠን በሊትር			አፈፃፀም በመቶኛ		
		ስም	ዞን	ወረዳ	ቀበሌ	ናፍጣ	ቤንዝን	ኬሮሰን	ናፍጣ	ቤንዝን	ኬሮሰን	ናፍጣ	ቤንዝን	ኬሮሰን

ፎርሙን የሞላው

ስም ፡- _____

ፊርማ ፡- _____

ስልክ ፡- _____

ቀን ፡- _____

ያረጋገጠው ኃላፊ

ስም ፡- _____

ፊርማ ፡- _____

ስልክ ፡- _____

ቀን ፡- _____

Petroleum and Energy Authority

ማደያ በሌለባቸው ቦታዎች የነዳጅ ችርቻሮ ንግድ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

ቅፅ 3 በቸርቻሪው ነጋዴ የሚሞላ

የቸርቻሪው ነጋዴ ስም..... የሚገኝበት ቦታ/ቀበሌ..... ስልክ ቁጥር.....

ተ.ቁ	ከማደየው የተጫነበት ቀን	የተገዛው የነዳጅ መጠን በሊትር			የተሸጠው የነዳጅ መጠን በሊትር			አፈፃፀም በመቶኛ			ምርመራ
		ናፍጣ	ቤንዝን	ኬሮሰን	ናፍጣ	ቤንዝን	ኬሮሰን	ናፍጣ	ቤንዝን	ኬሮሰን	

ፎርሙን የሞላው

ስም ፡- _____

ፊርማ ፡- _____

ስልክ ፡- _____

ቀን ፡- _____

ያረጋገጠው ኃላፊ

ስም ፡- _____

ፊርማ ፡- _____

ስልክ ፡- _____

ቀን ፡- _____